የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፭
አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

13th Year No. 45
ADDIS ABABA 23 July, 2007

ማ ው ጫ

አዋጅ ቁጥር ፭፻፴፱/፲፱፻፺፱ ዓ.ም

ለሦስተኛው የመንገድ ዘርፍ ልማት ድጋፍ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም ዐቀፍ የልማት ማኀበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ…. ገጽ ፫ሺ፮፻፹፫

CONTENTS

Proclamation No. 539/2007

International Development Association Financing Agreement for Third Road Sector Development Support Project Ratification Proclamation …. Page 3683

## አዋጅ ቁጥር ፭፻፴፱/፲፱፻፺፱

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለሦስተኛው የመንገድ ዘርፍ ልማት ድጋፍ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ፩፻፵፰ሚሊዮን ፯፻ሺ ኤስ.ዲ.አር /አንድ መቶ አርባ ስምንት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር/ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማህበር መካከል እ.ኤ.አ. ጁን ፰ ቀን ፪ሺ፯ በአዲስ አበባ ከተማ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለሦስተኛው የመንገድ ዘርፍ ልማት ድጋፍ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም ዐቀፍ የልማት ማኀበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፴፱/፲፱፻፺፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO.539/2007.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE FINANCING AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

**WHEREAS,** a Financing Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia loan in an amount not exceeding SDR 148,700,000 (one hundred forty eight million seven hundred thousand special Drawing Rights) for financing Third Road Sector Development Support Project was signed in Addis Ababa on the 8th day of June 2007;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 21st day of June, 2007;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Financing Agreement for Third Road Sector Development Support Project Ratification Proclamation No. 539/2007."

## ፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ.ኤ.አ. ጁን ፰ ቀን ፪ሺ፯ በአዲስ አበባ ከተማ የተፈረመው ቁጥር 4315-ET የብድር ስምምነት ፀድቋል።

## ፫. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፩፻፵፰ሚሊዮን፯፻ሺ ኤስ.ዲ.አር /አንድ መቶ አርባ ስምንት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር/ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ የሚያስችል ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

## ፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 2. Ratification of the Agreement

The Financing Agreement No. 4315-ET signed in Addis Ababa on the 8th day of June 2007 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

## 3. Power of the Minister of Finance and Economic Development

The Minister of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the credit amount of 148,700,000 (one hundred forty eight million seven hundred thousand special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Financing Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall come into force up on Publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 23 day of July, 2007**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**